## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 244188

ጥቅምት 03 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ረታ ቶሎሳ

በእወቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ኑረዲን ከድር

አመልካች፡- ሴቭ ዘ ችልድረን ኢንተርናሽናል ጂንካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ መስፍን ደሴ

2ኛ. አቶ ድሪባ ተስፋዬ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ መዝገቡ በዳኞች የእረፍት ጊዜ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በ13/07/2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጂንካ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 20606/14 መጋቢት 26 ቀን 2014 ዓ.ም የሠጠውን ውሳኔ የደቡብ ኦሞ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 17265 ሰኔ 06 ቀን 2014 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 40707 የካቲት 13 ቀን 2015 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በማጽናት መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለታቸው ሲሆን ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ከሳሾች ሆነው አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ሆነው በአሰሪና ሰራተኛ ህግ ጉዳይ ተከራክረዋል፡፡

በስር ፍ/ቤት ተጠሪዎች በቀን 03/01/2014 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከጥቅምት 09 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ በሰው ሀብት አስተዳደር እና አቅርቦት ሰንሰለት ኦፊሰርነት ላልተወሰነ ጊዜ ተቀጥረው በወር ደሞዝ ብር 13,464.90 (አስራ ሶስት ሺ አራት መቶ ስልሳ አራት ብር ከዘጠና ሳንቲም) 2ኛ ተጠሪ በ2007 ዓ.ም ለተወሰነ ጊዜ ከተቀጠሩ በኋላ ከየካቲት 22 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ላልተወሰነ ጊዜ ውላቸው ተራዝሞ በወር ደሞዝ ብር 33,448.28 (ሰላሳ ሶስት ሺ አራት መቶ አርባ አራት ብር ከሃያ ስምንት ሳንቲም) እየተከፈላቸው ሲሰሩ የነበሩ መሆኑን ገልጸው ሆኖም ግን አመልካች ድርጅት ታህሳስ 21 ቀን 2012 ዓ.ም እና ከጥር 5 እስከ ጥር 8 ቀን 2012 ዓ.ም ላልተሰራ የመስክ ስራ ያለአግባብ አበል ከፍላችኋል በሚል ተጠሪዎችና ለሌሎች ሰራተኞች በኢሜል አድራሻችን ጠይቆን መልሳችንን በጽሁፍ በቀን 17/07/2013 ዓ.ም ሰጥተን በዚሁ ቀን ደርሶት እያለ ድርጊቱ ከተፈጸመ እና  ሪፖርቱም ለአመልካች ድርጅት ተልኮ ካወቀው ከአንድ አመት በኋላ፣ በጉዳዩ ላይ ምላሽ ስጡ ብሎ ምላሽ ሰጥተን ከደረሰው ደግሞ ከ4 ወር ከ18 ቀን በኋላ ነሃሴ 04 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውላችንን በህገ ወጥ መንገድ ያቋረጠ በመሆኑ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሎን ወደስራችን እንዲመልሰን በአማራጭም ከህገወጥ የስራ ስንብት ጋር የተያያዙ ክፍያዎችን በማስላት ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ባቀረበው መልስ ለተጠሪዎች ስንብት ምክንያት የሆነው ከግዥ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ኮሚሽን ተከፍሏል የሚልና ተገቢ ያልሆነ የአበል ክፍያ ተፈጽሟል የሚል ጥቆማ በመቅረቡ ሲሆን ጥቆማ በቀረበበት ቀን ጥቆማውን የሚያጣራ መርማሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ በተለይም አበሉን የሚመለከተው ጉዳይ በድጋሚ ማጣራት ተደርጎበት ሀምሌ 09 ቀን 2013 ዓ.ም ለበላይ ሃላፊ በተላከው ሪፖርት ተጠሪዎች ይህንን ከስራ ያለማስጠንቀቂያ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት መፈጸማቸው የተረጋገጠ በመሆኑ በህግ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሳያልፍ ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው፡፡ ተጠሪዎች የስራ መሪ በመሆናቸው ጉዳዩ በፍታብሔር ህግ የሚዳኝ ነው፡፡ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ውል የፈጸሙት ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑና ያልተከፈላቸው ቀሪ ህጋዊ ክፍያ የሌለ በመሆኑ እንዲከፈሏቸው የጠየቁት ክፍያ ሊከፈላቸው የሚገባበበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ቢባል እንኳ ክፍያ ሊከፈላቸው የሚገባው በፍታብሄር ህጉ አግባብ ነው፡፡ አመልካች በተጠሪዎች እምነትና መተማመን የሌለው በመሆኑ ተጠሪዎች ወደ ስራ ሊመለሱ አይገባም ስንብቱም ህጋዊ በመሆኑ አመልካች ሊከፍል የሚገባው ክፍያ የለም ተብሎ ይወሰንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃዎች መርምሮ ተጠሪዎች የቅጥር ውል የፈጸሙት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት በመሆኑ ተጠሪዎች ሰራተኞች እንጂ የስራ መሪ ሊባሉ ስለማይችሉ ጉዳያቸው መታየት ያለበት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት ነው፡፡  አመልካች ተጠሪዎች ፈጽመውታል ያለውን

ያላግባብ የ4 ቀን አበል የወሰዳችሁ እና ሌሎች ሰራተኞችም እንዲወስዱ አድርጋችኋል ያለበትን ጥፋት በመጀመሪያ ካጣራ በኋላ በድጋሚ ሲያጣራ ላቀረበው መጠይቅ ተጠሪዎች በጽሁፍ የሰጡት ምላሽ በቀን 17/07/2013 ዓ.ም ለአመልካች ደርሶት አመልካች ተጠሪዎች ጥፋተኛ ናቸው በማለት የስንብት ደብዳቤ የሰጠው ነሃሴ 04 ቀን 2013 ዓ.ም ጥፋታቸውን ካወቀ ከ4 ወር ከ18 ቀን በኋላ መሆኑ በመረጋገጡና ይህም በአዋጁ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የሰጠው ውሳኔ በመሆኑ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው፡፡ ተጠሪዎችን ወደ ስራ መመለስ ከአመልካች ጋር መልካም የስራ ግንኙነት ሊፈጥር የማይችል በመሆኑ ወደ ስራ ሊመለሱ አይገባም በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ 4 አመት ከ10 ወር 2ኛ ተጠሪ 6 አመት ከ4 ወር ያገለገሉ በመሆኑ በዚሁ ልክ የስራ ስንብት ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ክፍያ ለ1ኛ ተጠሪ የ2 ወር ደሞዝ ለ2ኛ ተጠሪ የ1 ወር ደሞዝ፣ ካሳ የ180 ቀን ደሞዝ፣ አመልካች ሊከፍል የሚገባውን ክፍያ ከ7 ቀን በላይ ያዘገየባቸው በመሆኑ የ3 ወር ደሞዝ፣ የአመት ረፍት አመልካች ባመነው ቀን ልክ በገንዘብ ቀይሮ ለተጠሪዎች ለያንዳንዳቸው ሊከፍል ይገባል በማለት የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብትን ለተጠሪዎች በመጠበቅ ወስኗል፡፡

አመልካችም በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮብናል በማለት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለደቡብ ኦሞ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት በፍ/ሥ/ስ/ህ/ቁ. 377 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡ በኋላም ጉዳዩ በሰበር የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካችም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት በቀን 13/7/2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ተጠሪዎች ይሰሩ የነበረው ስራ የስራ መሪ መሆናቸውን የሚያሳይ ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት ስራ መሪዎች አይደሉም በማለት መወሰኑ አግባብ አይደለም፤ ተጠሪዎች የይርጋ ክርክር ሳያነሱ ፍ/ቤቱ በራሱ አንስቶ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፤ ተጠሪዎች የስራ መሪ በመሆናቸው የ30 ቀናት ይርጋው ተፈጻሚነት የሌለው በመሆኑና ተጠሪዎች ፈጸሙ ለተባለው ጥፋት ምላሽ የሰጡበት ቀን የማጣራት ሂደቱ አካል ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት ተጠሪዎች ጥፋት መፈጸማቸው የተረጋገጠበት ቀን አድርጎ በመውሰድ እንዲሁም አመልካች ለስንብት ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ሁለት ጊዜ በአግባቡ በማጣራት በርግጠኝነት ማወቅ የቻለው እ.አ.አ. ጁላይ 16/2021 ሲሆን የስንብት እርምጃውን የወሰደው እ.አ.አ. ኦገስት 10/2021 በመሆኑ 30 ቀናት ሳያልፍ የወሰነ በመሆኑ በይርጋ ሊታገድ የማይገባው ሆኖ እያለ የአመልካች እርምጃ የመውሰድ መብት በይርጋ ታግዷል መባሉ አግባብነት የለውም፡፡

የስር ፍ/ቤት ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ለማለት የቻለው ተጠሪዎች እና ሌሎች ሰራተኞች ላልተሰራ ስራ አበል መውሰዳቸውን አረጋግጫለው በማለት ሲሆን አመልካች ሁሉንም ተገቢ ያልሆነ አበል የወሰዱ ሰራተኞችን ሁሉ ማሰናበት ሲገባው ተጠሪዎችን ብቻ ለይቶ ማሰናበቱ ህገ ወጥ ነው በማለት መሆኑ ተቀባይነት የለውም፤ 1ኛ ተጠሪ ለተወሰነ ጊዜ እስከ ዲሴምበር 31/2021 እ.አ.አ ድረስ ብቻ የውል

ጊዘው የሚቆይ በመሆኑ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ቢባል እንኳ ሊከፈለው የሚገባው እስከዚሁ ጊዜ ላለው ብቻ መሆን ሲገባውና አመልካችም ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ የሌለበት ሆኖ እያለ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ይከፈለው መባሉ አግባብ አይደለም፤ አመልካች ያዘገየው ክፍያ በሌለበትና የአመት እረፍታቸውንም ተጠሪዎች ለመውሰድ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ያልተከፈላቸው ሆኖ እያለ እንዲሁም የ10 ቀን ይከፈለን የሚል ዳኝነት ባላቀረቡበት የስር ፍ/ቤት የ10 ቀን ክፍያ የዘገየ በመሆኑ የ3 ወር ደሞዝ ይከፈላቸው በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት በመሆኑ እንዲሻርልን እንጠይቃለን የሚል ነው፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎትም በስር ፍ/ቤት አመልካች የአሁን ተጠሪዎች የስራ መሪ አይደሉም የተባለበትና ይከፈል ተብለው የተወሰኑት ክፍያዎች የተወሰኑበት አግባብ መጣራት ያለበት በመሆኑ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ግራ ቀኙም መልስና የመልስ መልስ ይቀባበሉ ሲል አዟል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ መሰረት ተጠሪዎች በ14/08/2015 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ ተጠሪዎች የተቀጠርነው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.377/1996 መሰረት በመሆኑ፣ በስራ ቅጥር ውላችን ላይ ከስራ ውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ ተፈጻሚነት ያለው ህግ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ስለመሆኑ የተመለከተ በመሆኑ፣ ምስክሮችም ሆኑ በስር የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ የቀረቡ የስራ መዘርዝር ማስረጃዎችም ተጠሪዎች የስራ መሪ ስራዎችን እንደማይሰሩ ያረጋገጡ በመሆኑ፣ አመልካች ለተጠሪዎች በጻፈው ደብዳቤ የ1ኛ ተጠሪ የስራ ውል ከየካቲት 21 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የ2ኛ ተጠሪ ከሃምሌ ወር 2010 ዓ.ም ጀምሮ ላልተወሰነ ጊዜ የተራዘመ በመሆኑ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩና የስራ መሪ ሊባሉ የማይችሉ ናቸው፡፡ አመልካች ተጠሪዎችን ከስራ ሲያሰናብት ለያንዳንዳችን የ10 ቀን ደሞዝ ያልከፈለ በመሆኑ የአመት እረፍት ክፍያም ለእያንዳንዳችን የ17 ቀን ሳይከፍል ያለምንም ምክንያት ያዘገየ በመሆኑ ለዘገየ ክፍያ በሚልና ሌሎች ክፍያዎች በስር ፍ/ቤት የተወሰኑበት አግባብ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ውሳኔው እንዲጸናልን እንጠይቃለን የሚል ነው፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ጭብጥ መሰረት በማድረግ በውሳኔው ላይ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡አመልካች ተጠሪዎች የስራ መሪዎች በመሆናቸው ክርክሩ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት ሊመራ አይገባም በማለት ያቀረበውን ክርክር በተመለከተ የስር ፍርድ ቤቶች ለተጠሪዎች የተሰጣቸው አመልካች ለክርክሩ ይረዳኛል በማለት እንዲቀርብለት የጠየቀው የስራ መዘርዝር ተጠሪዎች ሰራተኞችን የሚቆጣጠሩ፤የሚያስተዳድሩ፤ጥፋት ሲያጠፉ የዲሲሰፒሊን እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን የማያሳዩ መሆኑን፤ከዚህ ውጪ ተጠሪዎች የስራ መሪዎች ለመሆናቸው የሚያስረዳ የሰው ሆነ የሰነድ ማስረጃ አለመቅረቡን በውሳኔያቸው ላይ አመልክተዋል፡፡የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን

በመስማት፤በመመርመርና በመመዘን ተጠሪዎች የስራ መሪዎች አይደሉም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ በዚህ ችሎት ሊለወጥ የሚችለው የስር ፍርድ ቤት ከማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር የፈፀሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት ከተገኘ ብቻ ሲሆን ይህ ችሎት ባደረገው ምርመራም የስር ፍርድ ቤቶች የቀረቡትን ማስረጃዎችን በመመርመር ተገቢውን ማጣራት በማድረግ በደረሱበት መደምደሚያ ላይ ከማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስላላገኘን አመልካች ይህንን በተመለከተ ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

ስንብትን በተመለከተም ጥፋትን መሰረት በማድረግ አሰሪው የስራ ዉል ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ ያለዉ መብት ጥፋት መፈጸሙን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ከሚቆጠር 30 የስራ ቀናት በኋላ በይርጋ የሚታገድ መሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(3) ተደንግጓል፡፡ይሁንና "…የስራ ውሉ የሚቋረጥበትን ምክንያት መኖሩን ካወቀ …" በሚል በህጉ የተመለከተውን ሀረግ መነሻ በማድረግ የተፈጸመዉ ጥፋት ለማጣራት እና ለማረጋገጥ ሲባል የሚወሰደዉ የማጣራት ሂደት የሚፈጀዉ ጊዜ ከግምት ሊወሰድ የሚገባ ስለመሆኑ ሰበር ችሎቱ በሰ/መ/ቁ.53358 እና ተመሳሳይ መዝገቦች አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ የ30 የስራ ቀናት አቆጣጠር መነሻ ተደርጎ የሚወሰደው ጥፋቱ የተፈፀመበት ቀን ሳይሆን ጥፋት መፈፀሙን አሰሪው ካረጋገጠበት ቀን ጀምሮ መሆኑን ከድንጋጌውና ድንጋጌውን መሰረት አድርጎ ከተሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም አጠቃላይ ይዘት የምንረዳው ነው፡፡

በዚህም ጉዳይ ተጠሪዎች አላግባብ አበል ተከፈለ የተባለው ከታህሳስ 18 እስከ ታህሳስ 21 ቀን 2012 ዓም እና ከጥር 5 እስከ ጥር 8 ቀን 2012 ዓም ድረስ ሆኖ ይሄንንም ሁኔታ የአመልካች ድርጅት ኦዲተሮች ጥቆማ ደረሰን ብለው ከመጋቢት 22 እስከ መጋቢት 27 ቀን 2013 ዓም ድረስ ሰራተኞችን ጠይቀው ቃላቸውን ተቀብለው ከሄዱ 4 ወር በኋላ ከድርጊቱ መፈፀም 1 አመት ከ8 ወር በኋላ ነሀሴ 04 ቀን 2013 ዓም ከስራ እንዲሰናበቱ መደረጉ በአዋጁ አንቀፅ 27(3) መሰረት ስንብቱን ህገወጥ የሚያደርገው መሆኑን ጠቅሰው ስንብቱ ህገወጥ ተብሎ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሏቸው ወደስራቸው እንዲመለሱ አልያም ከህገወጥ የስራ ስንብት ጋር የተያያዙ ክፍያዎችን አመልካች እንዲከፍላቸው እንዲወሰንላቸው ሲጠይቁ አመልካች በበኩሉ ለስንብቱ ምክንያት የሆነውን ህገወጥ ድርጊት መፈፀሙን ያረጋገጥኩት ዳግም ሪፖርቱ ከቀረበለኝ ሀምሌ 09 ቀን 2013 ዓም ጀምሮ በመሆኑ የማሰናበቻ ህጋዊ መብቴን በአዋጁ አንቀፅ 27(3) መሰረት ላጣ አይገባም በማለት መከራከሩን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡በመሰረቱ ተጠሪዎች ክርክራቸውን ለማስረዳት ካቀረቧቸው ሶስት ምስክሮች ውስጥ 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች ተጠሪዎች ራሳቸው ሲሆን ተጠሪዎችን ጨምሮ 3ኛ ምስክሩ የአመልካች ድርጅት ኦዲተሮች ጥቆማ ደረሰን ብለው ከመጋቢት 22 እስከ መጋቢት 27 ቀን 2013 ዓም ድረስ ሰራተኞችን ጠይቀው ቃላቸውን ተቀብለው ሄዱ በማለት ከማስረዳታቸው ውጪ ይህ በመጋቢት ወር 2013 ዓም የተደረገው ማጣራት የመጨረሻ የማጣራት ሂደት ሆኖ የተጠሪዎች ተሳትፎ ተለይቶ የተጠሪዎች ተጠያቂነት በሪፖርቱ ተለይቶ የተረጋገጠበት መሆኑን በዝርዝር ለይተው አላስረዱም፡፡

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ከዚህ ይልቅ የአመልካች 1ኛ ምስክር የተጠሪዎችን ተሳትፎ በአግባቡ የለየ በተለይም ለወ/ሮ አያልነሽ ከተከፈለው አበል ጋር በተያያዘ ተጠያቂነት ያለበት ማን እንደሆነ የለየ የኦዲት ሪፖርት ግለሰቧን ጭምር በመጠየቅ ያዘጋጁት በድጋሚ ማጣራቱ መሆኑን ማስረዳታቸው አመልካች ለስንብቱ ምክንያት ነው ያለውን ጥፋት አረጋገጠ ሊባል የሚችለው ሀምሌ 09 ቀን 2013 ዓም በቀረበው ሪፖርት መሆኑን ያሳያል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪዎችን ነሀሴ 04 ቀን 2013 ዓም ያሰናበተው በአዋጁ አንቀፅ 27(3) ከተመለከተው የ30 የስራ ቀናት በኋላ ነው ተብሎ በዚሁ ነጥብ ምክንያት ስንብቱ ህገወጥ ነው የሚባልበት አግባብ ሳይኖር የስር ፍርድ ቤቶች ስንብቱ ህገ ወጥ በማለት ከህገ ወጥ ስንብት ጋር የተያያዙ ክፍያዎችን አመልካች ለተጠሪዎች እንዲከፍል መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጂንካ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 20606/14 መጋቢት 26 ቀን 2014 ዓ.ም የሠጠው ውሳኔና ይህንን ውሳኔ በማፅናት የደቡብ ኦሞ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 17265 ሰኔ 06 ቀን 2014 ዓ.ም እንዲሁም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 40707 የካቲት 13 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡የስር ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪዎች ላይ ነሀሴ 04 ቀን 2013 ዓም በተፃፈ ደብዳቤ የፈፀመው ስንብት ህገ ወጥ ነው በማለት አመልካች ለተጠሪዎች የስራ ስንብት ክፍያ፤የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ፤ካሳ እና ክፍያ ለዘገየበት ክፍያ እንዲከፍላቸው የሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡አመልካች ባመነው መሰረት ለተጠሪዎች የአመት እረፍት ክፍያ እንዲፈፅም የሰጠው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

2. የጂንካ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጉዳዩን መዝገብ በማንቀሳቀስ አመልካች ለስንብቱ ምክንያት አድርጎ ከጠቀሳቸው ነጥቦች አንፃር አመልካች ተጠሪዎችን ከስራ ያሰናበተው በህጉ አግባብ በበቂ ምክንያት ነው? ወይስ አይደለም? ስንብቱ ህጋዊ ነው ከተባለ ውጤቱ ምን ሊሆን ይገባል? ስንብቱ ህገወጥ ነው ከተባለስ አመልካች ለተጠሪዎች ሊከፍላቸው የሚገባው ክፍያ አይነቱ እና መጠኑ ምን ሊሆን ይገባል? ክፍያ ለዘገየበት ክፍያ አመልካች ለተጠሪዎች ሊከፍል ይገደዳልን? ሊከፍል ይገደዳል ከተባለስ መጠኑ ምን ያህል ሊሆን ይገባል? የሚሉትንና ተያያዥ ጭብጦችን በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር፤ተገቢውን ማጣራት በማድረግ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡

3.ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

**ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡**

*ማ ስታወሻ፦ ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

መ/ዐ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም